# የፌዴራል የፍትህና ህግ ኢንስቲትዩት

# የሠራተኞች የአደጋ መከላከያ ቁሳቁሶችና አልባሳት አሰጣጥና አጠቃቀም

## መመሪያ ቁጥር 873/2014

አዲስ አበባ
2014 ዓ.ም

# መመሪያ ቁጥር 873/2014 ዓ.ም

## የፌዴራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት ሠራተኞች የአደጋ መከላከያ

## ቁሳቁሶችና አልባሳት አሰጣጥና አጠቃቀም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 42(2) ላይ ‹‹ሰራተኞች ጤናማና አደጋ የማያደርስ የስራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው›› በሚል የተደነገገውን፣ እንዲሁም የስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ በፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ውስጥ የተደነገገውን ተግባራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ በማሻሻል የሰራተኞችን ደህንነትና ጤንነት በመጠበቅ የስራ ብቃት ማጎልበት፣ የስራ ቦታን ለሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት በሚስማማ መልኩ ማዘጋጀት፣ ማደራጀት፣ ማሻሻልና መጠበቅ እንዲሁም መስሪያ ቤቱ /ተቋሙ/ በጎ በሆነ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተመስርቶ አመርቂ የስራ ውጤት እንዲያስመዘግብ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች የሚባሉት ቁሳቁሶች እንደ እጅ ጓንት፣ ማስክ፣ ሴፍቲ ጫማ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ በትክክለኛና በአግባቡ መጠቀም ሰራተኞችን ከተለያዩ አደጋዎች ማለትም ከአካላዊ፣ ስነልቦናዊና አዕምሯዊ፣ ከረቂቅ ተህዋሲያንና ከመሳሰሉት መከላከል የሚያስችል የሚያስችል በመሆኑ፤

አንድ ሠራተኛ ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት እንደሥራው ባህሪ ሙሉ በሙሉም ይሁን በከፊል ጤንነቱን እና ደህንነቱን ከተለያዩ የሥራ ቦታ አደጋ፣ የጤና ጠንቆችና ጉዳቶች ለመከላከል የሚረዱ የአደጋ መከላከያና እንዲሁም አደጋ ቢከሰት የሚደርሰውን አስከፊ የጉዳት መጠን ሊቀንሱ የሚችሉ መከላከያ መሳሪያዎችን የሥራ መሳሪያዎች ወይም ልብሶች መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ፤

በፌዴራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሰረት እያንዳንዱ የመንግስት መሥሪያ ቤት የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶችን ለሠራተኞች የማቅረብና ስለአጠቃቀማቸው መመሪያ የመስጠት ኃላፊነት የተሰጠው በመሆኑ፤ ሥራ በመሥራት በሚገኝ ሠራተኛ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መከላከሉ ወይም የጉዳቱን መጠን መቀነሱ የሚወሰነው ሥራው የሚጠይቀውን የመከላከያ መሳሪያዎች አይነት በመለየትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ሲቻል በመሆኑ፤ በኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም ባለመቻላቸው፣ የግንዛቤ እጥረት እና ምቹ የሆነ የስራ አካባቢ ባለመኖሩ ለቀላል፣ መካከለኛና እስከ ህይወት መጥፋት ለሚዳርግ አደጋ ተጋልጠው እንደሚገኙ ግንዛቤ የተወሰደ በመሆኑ፤

በሠራተኞች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ወይም የሚደርሱ የአደጋና የጤና ችግሮችን ቀድሞ ለመከላከል እንዲያስችል ከሲቪል ሰርቪስ ኪሚሽን የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፣ ደንብ ልብስ እና ፕሮቶኮል አሰጣጥ በተመለከተ በ2000 እና በ2011 ዓመት የወጡ መመሪያዎችን፣ የመንግስት ሠራተኞችን አዋጅ እና የተለያዩ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት በተመለከተ የተዘጋጁ ጽሁፎችን በማገናዘብ የፌዴራል የፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት በኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1071/2010 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የፌዴራል የፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት የአደጋ መከላከያ ቁሳቁሶች፣ የደንብ እና የፕሮቶኮል አልባሳት አሰጣጥ እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 873/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "ጤና" ማለት በበሽታ አለመያዝ ብቻ ሳይሆን ፍፁም የሆነ የአካል፤ የአእምሮና የማህበራዊ ኑሮ ደህንነት ነው፤

2) "አካባቢ" ማለት የእለት ከእለት ተግባሮችን የምናከናውንበት፣ የተለያዩ ስራዎችን የምንሰራበት፣ በዙሪያችን የምናየው፣ የምንተነፍሰው አየር፣ ውሃማ አካላትና ሌሎችንም የሚያጠቃልል ነው፤

3) "የስራ አካባቢ ደህንነት" ማለት ሰራተኛው በስራ አካባቢ በሚገለገልባቸው የስራ መሳሪያዎችና በሚከተላቸው የአሰራር ዘዴዎች ምክንያት ሊገጥሙት የሚችሉ አደጋዎችን የሚመለከት ነው፤

4) "የስራ አካባቢ ጤንነት" ማለት ሰራተኛው ከስራ አካባቢው ወይም ከተመደበበት የስራ መደብ ባህሪ ሊመነጩ የሚችሉና በጤንነት ላይ ችግር ሊያደርሱ የሚችሉ ሁኔታዎችን የሚመለከት ነው፤

5) "የስራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት በለሙያ" ማለት በአካባቢ ጤና አጠባበቅ ወይም በስራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት የተመረቀ ከስራ ጋር የተያያዙ የጤንነትና የደህንነት ጉዳዮችን የሚመከታተል ባለሙያ ነው፤

6) "የስራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ" ማለት በስራ አካባቢ የሚከሰቱ ወይም ከስራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ኬሚካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ማህበራዊ፣ ፊዚካላዊና ስነ ህይወታዊ ንጥረ ነገሮችን በመከላከልና በመቆጣጠር ሰራተኞች ለአደጋ እንዳይጋለጡ በማድረግ ሳይንሳዊ፣ ቴክኖሎጂካዊና አስተዳደራዊ ዘዴዎችን በመጠቀም የሰራተኞችን ጤንነትና ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል አሰራር ነው፤

7) “የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ጉድለት” ማለት አንድ ሰራተኛ በሚሰራበት የሚገኝ በአካላዊ ዕድገት፣ በጤና ወይም በአኗኗር ዘይቤ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል ማናቸውም ሁኔታ ነው፤

8) “ሰራተኛ” ማለት በኢንስቲትዩቱ በቅጥር ወይም በዝውውር በቋሚ ወይም በኮንትራት ተመድቦ እየሰራ የሚገኝ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

9) “የሥራ መደብ” ማለት በአንድ የመንግስት ሠራተኛ ሙሉ የሥራ ጊዜ እንዲከናወኑ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ናቸው፤

10) “በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት” ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት ነው፤

11) “በሥራ ላይ የደረሰ አደጋ” ማለት ማንኛውም ሠራተኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ምክንያት የሚመጣ አደጋ ነው፤

12) “በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ” ማለት የመንግሥት ሠራተኛው ከሚሠራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሳ በሽታን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ምክንያት የደረሰ የጤና መታወክ ነው፤

13) “የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች” የሚባሉት ሰራተኛው ስራውን በሚሰራበት ወቅት ከጤና ጠንቆችና አደጋዎች እራሱን ለመከላከል የሚለበሱ፣ የሚታሰሩ፣ የሚደረጉ እና የሚሸጉጡ የስራ መሳሪያዎችና የስራ ልብሶች ናቸው፤

14) “የሥራ ላይ የጤና ጠንቆች” ማለት በሥራ ላይ የሚገኙ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሠራተኛውን በሥራ ምክንያት ለሚመጣ በሽታ ወይም ጉዳት የሚዳርጉ በንክኪ፣ በትንፋሽ ወይም በሌሎች አጋላጭ መንገዶች ሳቢያ የህመም ወይም የአካል ጉዳት የሚያደርሱ ወይም የስራ አካባቢን የሚበክሉ ንጥረ ነገሮች፣ ቁሶች፣ መሳሪያዎች ወይም ሥነ-ህይወታዊ ተውሳኮች ናቸው፤

15) “ማስክ” ማለት ሠራተኛው ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት በአፍና አፍንጫ ከሚገቡ አቧራ፣ ብናኝ፣ ኬሚካል፣ ጀርሞች እና ሌሎች የጤና ጠንቆች ለመከላከል የሚረዳ ከጨርቅ፣ ከጥጥ መሰል ወይም ከፕላስቲክ የተሰራ መሸፈኛ ነው፤

16) “ጎግል” ማለት ዓይንን ከአቧራ፣ ከብናኝ፣ ከኬሚካላዊ ፍንጣሪ፣ ከብየዳ ፍንጣሪ እና ከጨረር ለመከላከል የሚረዳ ከፕላስቲክ የተሰራ የአደጋ መከላከያ መሳሪያ ነው፤

17) “ሙሉ የሥራ ቱታ” ማለት ከፖሊስተር ካኪ (6000) ጨርቅ የሚዘጋጅ ሆኖ ሰራተኞች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ከጤና ጠንቅ፣ ከአቧራ እና ከብናኝ እንዲሁም

የልብስን መቆሸሽ የሚከላከል በልብስ ላይ ተደርቦ የሚለበስ ቀለሙና ዓይነቱ ተመሳሳይ የሆነ የስራ ልብስ ነው፤

18) “ካፖርት” ማለት ከሱፍ፣ ከጥጥ ወይም ከጥጥ ሴንቴቲክ የተሰራ ሙቀት እንዲሰጥ ገበር ያለው በተለይ ለሌሊት ብርድ መከላከያ የሚያገለግል ቀለሙና ዓይነቱ ተመሣሣይ የሆነ ልብስ ነው፤

19) “3/4 ጋዋን” ማለት ከፖሊስተር ካኪ (6000) ጨርቅ የተሰራ በልብስ ላይ ተደርቦ የሚለበስ እና ቆሻሻ ወይም አቧራ የሚከላከል ቀለሙና ዓይነቱ ተመሣሣይ የሆነ ልብስ ነው፤

20) “ሽርጥ” ማለት ከፖሊስተር ካኪ (6000) ጨርቅ የተሰራ ሆኖ በስራ ላይ ቆሻሻ ወይም አቧራ ለመከላከል የሚለበስ ቀለሙና አይነቱ ተመሣሣይ የሆነ ልብስ ነው፤

21) “አጭር ቆዳ ጫማ” ማለት ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው ሆኖ ቁመቱ ከቁርጭምጭሚት የማያልፍ በቀላሉ ተንቀሳቅሶ ስራ ለማከናወን የሚረዳ በአገር ውስጥ ከቆዳ የተሰራ ቀለሙና ዓይነቱ ተመሣሣይ የሆነ ጫማ ነው፤

22) “ቡትስ ቆዳ ጫማ” ማለት ዚፕ ወይም ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው ሆኖ ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን እና ሰራተኞችን ከአደጋ ለመከላከል የሚረዳ በአገር ውስጥ ከቆዳ የተሰራ ቀለሙና ዓይነቱ ተመሣሣይ የሆነ ጫማ ነው፤

23) “የዝናብ ልብስ” ማለት ከሲንቴቲክ የተሰራ ዝናብ የማያስገባ ቀለሙና ዓይነቱ ተመሣሣይ የሆነ የዝናብ ልብስ ነው

24) “ዣንጥላ” ማለት የሚዘረጋና የሚታጠፍ ሆኖ በዝናብ ወቅት ዝናብን ለመከላከል የሚያገለግል መሳሪያ ነው፤

25) “የእጅ ጓንት” ማለት ከፕላስቲክ ወይም ከሴንቴቲክ ቆዳ የተሰራ ሆኖ በእጅ ላይ የሚጠለቅ ከቅዝቃዜ፣ ከአቧራ፣ ከስለታም ነገሮች እና ጉዳት ከሚያደርሱ ፍሳሾች ለመከላከል የሚያገለግል የሥራ መሳሪያ ነው፤

26) “የፀጉር መሸፈኛ ሻሽ” ማለት ላስቲክ ያለው በዕዳት ወቅት የጸጉር ንጽህናን እና ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ሻሽ ነው፤

27) “ፍራሽ” ማለት ከስፖንጅ የተዘጋጀ በሌሊት ሽፍት ስራ ወቅት ለማረፍ የሚያገለግል መሳሪያ ነው፤

28) “ብርድ ልብስ” ማለት በአገር ውስጥ የተመረተ ጥራቱን የጠበቀ ብርድን ለመከላከል የሚረዳ ልብስ ነው፤

29) “እንሶላ” ማለት በሀገር ዉስጥ የተመረተ ከብርድ ልብስ ስር የሚለበስና ለፍራሽ መሸፈኛ የሚያገለግል ልብስ ነዉ፤

30) “ትራስ” ማለት በአገር ውስጥ ከስፖንጅ የተመረተ ጥራቱን የጠበቀ ራስን ለማሳረፍ የሚረዳ መሳሪያ ነው፤

31) “የትራስ ልብስ” ማለት በአገር ውስጥ የተመረተ ጥራቱን የጠበቀ ለትራስ መሸፈኛ የሚያገለግል ልብስ ነዉ፤

32) “የደንብ ልብስ” ማለት የሥራ ልብስ ሆኖ አንድ የመንግስት ሠራተኛ በተመደበበት የሥራ መደብ ላይ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ እንደሥራው ፀባይ ለሠራተኛው መለያ ሆኖ እንዲያገለግል እንዲሁም ተገልጋይ በቀላሉ ለይቶ እንዲያውቀው የሚረዳ ቀለሙና አይነቱ ተመሳሳይ የሆነ ልብስ ነው፤

33) “ኮትና ሱሪ” ማለት ሱፍ ነክ ከሆነ ጨርቅ የሚሰፋ ቀለሙና አይነቱ ተመሳሳይ የሆነ ልብስ ነው፤

34) “ቀበቶ” ማለት በአገር ውስጥ ከቆዳ የተሰራ ሱሪን ወገብ ላይ ለማሰር (ለማጥበቅ) የሚረዳ መሳሪያ ነው፤

35) “ሸሚዝ” ማለት ቀለሙና ዓይነቱ ተመሳሳይ የሆነ ለሸሚዝ አገልግሎት የተዘጋጀ/ሬዲ ሜድ/ ልብስ ነው፤

36) “ከረቫት” ማለት ከኮትና ሱሪው ወይም ኮትና ጉርድ ቀሚስ ጋር የሚሄድ የተዘጋጀ/ሬዲ ሜድ/ የሆነ በአንገት ላይ የሚታሰር ልብስ ነው፤

37) “ካልሲ” ማለት በእግር ላይ የሚጠለቅ ጫማ በላዩ ላይ የሚደረግበት የተዘጋጀ/ሬዲ ሜድ የሆነ ልብስ ነው፤

38) በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ለሴትም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢንስቲትዩቱ ውስጥ የአደጋ መከላከያ ለሚጠቀሙ ሰራተኞችና የስራ ክፍሎች እና እንደአስፈላጊነቱ ለሁሉም ሰራተኞች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) ሰራተኞች የሚያስፈልገውን የሥራ ደህንነትና ጤንነት መከላከያ እንዲጠይቅና የተሰጠውንም በአግባቡ እንዲጠቀም ማድረግ፤

2) የሥራ ደህንነት መከላከያ ቁሳቁስ የሚያስፈልጋቸውና በዚህ መመሪያ ላይ ያልተካተቱ የስራ ዘርፎች ሲገኙ በስራ ጤንነትና ደህንነት ፕሮፌሽናል የስራ ዘርፉን አስጠንተው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማስፈቀድ ማስቻል፤

3) የሰራተኛውን የአደጋ መከላከያ አጠቃቀም ችሎታ ማሻሻልና ማሳደግ፤

4) የኢንስቲትዩቱን ሥራ አካባቢ ለሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት በሚስማማ መልኩ ለማዘጋጀት፣ ለማሻሻልና ለመጠበቅ፤

5) የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች ጊዜውን ጠብቀው እንዲሰጡ እና ለሁሉም ለአደጋ ተጋላጭ ሰራተኞች ተደራሽ ማድረግ፤

6) የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት በመጠበቅ የሥራ ብቃትን ማጐልበት፤

7) የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች በጐ በሆነ ማህበራዊ ሕይወት ላይ ተመሥርተው አመርቂ የሥራ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ማብቃት፡፡

## 5. የኢንስቲትዩቱ ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው፤

1) የሕግ ማሻሻያና ማሟያ የጥናትና ምርምር መርሐ-ግብር በመንደፍ የአገሪቱን የሕግ ሥርዓት ለማሟላትና አዳዲስ ሕጎችን ለማውጣት የሚያስችሉ ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፤

2) የፍትህ ሥርዓት እና የሕግ ትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን እና ሌሎች በፍትህ ዘርፉ ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ያቀናጃል፣ያስተባብራል፤

3) ከክልል የሕግ ጥናትና ምርምር እና ስልጠና ማዕከላት ጋር በመተባበር በአገር አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚነት የሚኖረው የስልጠና ካሪኩለም ያዘጋጃል፤

4) በፌደራል እና ከክልሎች ጋር በሚኖረው ትብብር መሠረት የራሳቸው ስልጠና ማዕከል በሌላቸው ክልሎች የፍትህ አካላት ውስጥ በማገልገል ላይ ለሚገኙ ባለሙያዎች የሥራ ላይ ስልጠና ይሰጣል፤

5) የፍትህ ሥርዓቱን ለሚያገለግሉ በግል ለተሰማሩ ጠበቆች ስልጠናዎችን ይሰጣል፤

6) የጥናትና ምርምር፣ የማማከር፣ ስልጠና እና የፈተና አገልግሎት ይሰጣል፤

7) የአገሪቱን የፍትህና የህግ መረጃ በማዕከል ያስባስባል፤ ያደራጃል፤ ተደራሽ ያደርጋል፤

8) የጥናትና ምርምር ውጤቶቹን ያሰራጫል፣ የሥልጠና ጽሁፎችን ያዘጋጃል፣ ያሰባስባል፣ ያሰራጫል፤

9) በፍትህ ዘርፉ ባለሙያዎች የቅድመ ስራ፣ የስራ ላይ እና ልዩ ስልጠናዎችን በመስጠት የዘርፉን አቅም ይገነባል፤ እንዲሁም ለዘርፉ አመራሮች ስልጠናዎችን ይሰጣል፣ወ.ዘ.ተ

## ክፍል ሁለት
## የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት የሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነቶች እና ጉዳት ለደረሰበት ሰራተኛ ስለሚከፈሉ ክፍያዎች

### 6. የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት የሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት

1) የሥራ ክፍሉ የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የአካባቢ ጤና አገልግሎትን ይከታተላል፣ ለሰራተኞች ከጤና ጋር የተያያዙ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤

ለ) የጤና ፖሊሲዎችና ህጎች በኢንስቲትዩቱ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ምግብና መጠጦች ከብክለት ነፃ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፤

ሐ) በውሃ፣ በምግብ ብክለትና በአካባቢ ጤና አገልግሎት ጉድለት ምክንያት የሚከሰቱትን የጤና ችግሮች ለመቆጣጠርና ጨርሶ እንዲጠፉ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ያመነጫል፤

መ) ከስራ ጋር በተያያዘ ሠራተኞች ላይ በሽታና አደጋ እንዳይደርስ የስራ አካባቢዎችና የመገልገያ መሳሪያዎች አስፈላጊውን ደረጃ እንዲይዙ ያደርጋል፤ አደጋ ወይም በሽታ ከደረሰም አስፈላጊውን መረጃ በመሙላት ለቅርብ ኃላፊው/ተጠሪው/ ያቀርባል፡፡

2) የሥራ ክፍሉ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የአካባቢ ጤና አጠባበቅን በተመለከተ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በኢንስቲትዩቱ ውስጥ በትክክል ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ለኃላፊው ሪፖርት ያደርጋል፤

ለ) በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ተሰማርተው የሚሰሩ ሰራተኞች ለአደጋ እንዳይጋለጡ ማድረግ ያለባቸውን ጥንቃቄ እንዲያውቁ በአጫጭር ሥልጠና ግንዛቤ ይፈጥራል፤

ሐ) የስራ አካባቢዎች ስለሚሻሻሉበት ሁኔታ አጥንቶ ለሃላፊው ያቀርባል፤

መ) ለፅዳት ሰራተኞች እና ለሌሎች ሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች እንዲሟላ ማድረግና ለሰራተኞቹ መቅረባቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ) ፍሳሽ ቆሻሻ በአግባቡ እንዲወገድ ማድረግና የማይሰሩ እጅ መታጠቢያዎችና የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮችን እንዲሰሩ ያደርጋል፤

ረ) በስራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ዙሪያ ከሰራተኞች ለሚነሱ ጥያቄዎች መፍትሄ በመፈለግ ምላሽ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሰ) ቢሮዎች፣ የመሰብሰቢያ አዳራሾችና አንሶላዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ንፅህናቸው እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

ሸ) ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ እንዲወገድና ቆሻሻ ማቃጠያ ውስጥ እንዲቃጠል ይከታተላል፤

ቀ) በኢንስቲትዩቱ ቤቱ ውስጥ ያሉ የስራ ክፍሎችን በመለየት የደህንነትና ጤንነት መከላከያ መሳሪያዎች ለሚያስፈልጋቸው የስራ ክፍሎች ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመነጋገር እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤

በ) ከሚሰሩት ስራ ጋር ተያይዞ በአካልና በጤንነት ላይ አደጋ ሲደርስ ሁኔታው ወይም አደጋው ከሚሰራው ስራ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን አጣርቶና ለይቶ በመመዝገብ ለበላይ ሃላፊ ለውሳኔ ያቀርባል፤

ተ) ወደ ተቋሙ ገቢ የሚደረጉ አላቂና ቋሚ እቃዎች፤ ኬሚካሎች ወ.ዘ.ተ. በሰራተኞች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ መከታተልና የመገልገያ ቀናቸው ያለፈባቸውንና አገልግሎት የማይሰጡ ቁሳቁሶች ካሉ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ተለይተው እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡

## 7. በሥራ ምክንያት የሚመጣ አደጋ ወይም ጉዳት

በሥራ ምክንያት የሚመጣ አደጋ ወይም ጉዳት ማንኛውም ሰራተኛ ሥራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የደረሰበት ጉዳት ወይም አደጋ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል:-

1) ሠራተኛው ከሥራ ቦታው ወይም ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭም ቢሆን የአሠሪውን ህጋዊ ትዕዛዝ ሥራ ላይ ያውል በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳት፤

2) ሠራተኛው ከሥራው ጋር በተያያዘ ግዴታ የተነሳ ከሥራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ሥራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በሥራው ቦታ ወይም በድርጅቱ ግቢ ውስጥ እያለ የደረሰበት ማንኛውም ጉዳት፤

3) ሠራተኛው ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው ወደ ድርጅቱ ለሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ ተቋሙ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም ድርጅቱ ለዚሁ ተግባር በተከራየውና በግልፅ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰበት ማንኛውም ጉዳት፤

4) ሠራተኛው ሥራውን በማከናወን ላይ ባለበት ጊዜ በአሠሪው ወይም በሦስተኛ ወገን ድርጊት ምክንያት የደረሰበት ጉዳት፡፡

## 8. በሥራ ላይ ለሚደርሱ ጉዳት ወይም አደጋ ስለሚሰጡ ክፍያዎች

በሥራ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ወይም አደጋ በተመለከተ ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉትን የመፈፀም ግዴታ አለበት:-

1) ጉዳት ለደረሰበት ሠራተኛ የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ በጊዜው የመስጠት፤

2) ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ ተስማሚ በሆነ የመጓጓዣ ዘዴ በአቅራቢያው ወደሚገኘው የሕክምና ጣቢያ የማድረስ፤

3) በተጎጅ ላይ ለደረሰው አደጋ ወይም ጉዳት የሕክምና አገልግሎቱን ባገኘበት ተቋም በህክምና ቦርድ በተወሰነ ውሳኔ መሠረት የካሳ ክፍያ መፈፀም፡፡

## 9. የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ

በሥራ ላይ እያለ ጉዳት ለደረሰበት ሠራተኛ ለሚከተሉት የሕክምና አገልግሎቶች፡-

1) የጠቅላላና የልዩ ሕክምና እንዲሁም የቀዶ ሕክምና ወጪዎች፣

2) የሆስፒታልና የመድሃኒት ወጪዎች፣

3) የማንኛውም አስፈላጊ ሰው ሰራሽ ምትክ ወይም ተጨማሪ አካሎችና የአጥንት ጥገና ወጪዎች፤ ከታከመበት ሆስፒታል በሚያቀርበው ማስረጃ መሰረት ኢንስቲትዩቱ ይከፍላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የኢንስቲትዩቱና የሥራ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት፣ የሠራተኞች መብቶችና ግዴታዎች፣ የሥራ መሣሪያዎችና ቁሳቁስ ዓይነት አሰጣጥ እና አጠቃቀም

### 10. የሥራ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት

**እያንዳንዱ የሥራ ክፍል፡-**

1) በክፍሉ ውስጥ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች፣ የደንብና የፕሮቶኮል አልባሳት የሚያስፈልጋቸውን ሠራተኞች ዝርዝር በወቅቱ ለሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፤

2) የሚያስፈልጉትን የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፣ የደንብና የፕሮቶኮል አልባሳት በወቅቱ መቅረብ እና መሟላት የሚገባቸውን በዝርዝር ለግዥና ንብረት አስተዳደር እና ደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ አለበት፤

3) የክፍሉ ሠራተኞች የተሰጧቸውን የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፣ የደንብና የፕሮቶኮል አልባሳት በአግባቡ እየተጠቀሙ መሆኑን ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

### 11. የኢንስቲትዩቱ ኃላፊነት

**ኢንስትቲዩቱ፡-**

1) የሥራ ቦታው በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

2) ከየሥራ ክፍሎች የሚቀርቡ አስፈላጊ የሆኑ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ለሠራተኞች የማቅረብና ስለ አጠቃቀማቸው መመሪያ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

### 12. የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ግዴታ

በፌዴራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀው ሆኖ የኢንስቲትዩቱ ሠራተኛ፡-

1) ጤንነትንና ደህንነትን ለመጠበቅ የወጡ መመሪያዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፤
2) የተሰጡ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶችን በመጠቀም የደንብና የፕሮቶኮል አልባሳት በአግባቡ ለብሶ በሥራ ገበታው ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት፤

3) ለሥራ የተሰጠውን የአደጋ መከላከያ መሣሪያ ባለመጠቀም ለሚደርስበት ጉዳት በፌደራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ መሠረት ኢንስቲትዩቱን ተጠያቂ ሊሆን እንደማይችል የመረዳት ግዴታ አለበት፤

4) የተሰጠውን የደንብ እና የፕሮቶኮል አልባሳት ለሌላ አሳልፎ የሰጠ፣ የሸጠ ወይም ከዚህ መመሪያ ውጪ ሲጠቀም የተገኘ እንዲሁም የተሰጠውን የደንብ ወይም የፕሮቶኮል አልባሳት ያልተጠቀመ ሰራተኛ በዲሲፕሊን ግድፈት ተጠያቂነት እንዳለበት መረዳት አለበት፤

5) አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲገምት ለሚመለከተው የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ወዲያውኑ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 13. የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች መብት

1) በሥራ ወቅት የሚያስፈልጋቸውን የአደጋ መከላከያ ቁሳቁስ የመጠየቅና የማግኘት መብት አላቸው፡፡

2) ከአደጋ ነፃ በሆነ የሥራ አካባቢ የመስራት መብት አላቸው፡፡

3) አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎች በሥራ ቦታ አካባቢ መኖሩን ሲረዳ ለሚመለከተው የሥራ ኃላፊ የማሳወቅ እና የጥንቃቄ እርምጃ እንድወሰድለት የማድረግ መብት አለው፡፡

## 14. የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፣ የደንብ እና የፕሮቶኮል አልባሳት አሰጣጥና አጠቃቀም

1) ማንኛውም ሠራተኛ የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፣ የደንብ እና የፕሮቶኮል አልባሳት ለማግኘት በተፈቀደለት የሥራ መደብ ላይ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሲመደብ ይሰጠዋል፡፡

2) የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች እና የደንብ አልባሳት ከታሰበላቸው ዓላማ አኳያ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ለማስቻል ብትን ጨርቅ ተገዝቶ በመሥሪያ ቤቱ በኩል ተሰፍቶ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

3) በዓመት ሁለት የደንብ አልባሳት የሚያገኝ ሠራተኛ አንድ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያና ቀሪው ደግሞ በዓመቱ አጋማሽ ላይ ተሰፍቶ ይሰጠዋል፡፡

4) በተመሳሳይ የሥራ መደቦች የአደጋ መከላከያ፣ የደንብና የፕሮቶኮል አልባሳት የሚጠቀሙ ሠራተኞች የሚሰጧቸው አልባሳት ቀለም እና የጥራት ደረጃ አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

5) ለአደጋ መከላከያ መሣሪያ፣ የደንብ እና የፕሮቶኮል አልባሳት የሚያስፈልጉ ሠራተኞች የጨርቅ እና የጫማ ዓይነቶችና መጠናቸው እንዲሁም የንፅሕና መጠበቂያዎች ዓይነት መጠን፣ ለፅዳት ሠራተኞች የሚያስፈልጉ ዕቃዎች እና ኬሚካል ብናኝ በሚከሰትባቸው ቦታዎች ለሚሰሩ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 15፣ 16 እና በሠንጠረዥ 1፣ ሠንጠረዥ 2፣ ሠንጠረዥ 3፣ ሠንጠረዥ 4፣ ሠንጠረዥ 5 እና ሠንጠረዥ 6 በዝርዝር በተመለከተው ጊዜ፣ ዓይነት፣ ጥራት፣ መጠን እና ብዛት መሠረት ይሆናል፡፡

## 15. የጨርቅ ዓይነቶች

1) ለሥራ ቱታ፣ ለ¾ ጋዋን እና ለሸርጥ የሚያገለግለው ጨርቅ ዓይነት ፖሊስተር ካኪ 6000 ጨርቅ ይሆናል፡፡

2) ለብርድ መከላከያ የሱፍ ካፖርት የሚያገለግለው ጨርቅ ዓይነት ከሱፍ ወይም ከጥጥ ወይም የጥጥና ሴንቴቲክ ድብልቅ ከሆነ ጥሬ እቃ የተሰራ ጨርቅ ይሆናል፡፡

3) ለዝናብ ልብስ የሚያገለግለው የጨርቅ ዓይነት ከሴንቴቲክ የተሰራ ዝናብ የማያስገባ ጨርቅ ይሆናል፡፡

4) ለሙሉ ልብስ፣ ለኮት፣ ለሱሪ እና ለጉርድ ቀሚስ የሚያገለግለው የጨርቅ ዓይነት ሱፍ ነክ ጨርቅ ይሆናል፡፡

## 16. የጫማ ዓይነቶች

የሚሰጠው ጫማ፡-

1) ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው ሆኖ ቁመቱ ከቁርጭምጭሚት የማያልፍ ከቆዳ የተሰራ አጭር ጫማ ይሆናል፤

2) ዚፕ ወይም ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው ሆኖ ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን ከቆዳ የተሰራ ቡትስ ጫማ ይሆናል፤

3) ማሰሪያ ያለው ወይም የሌለው ሆኖ ቁርጭምጭምትን የሚሸፍን ከፕላስቲክ የተሰራ ቡትስ ጫማ ይሆናል፡፡

## ሠንጠረዥ1.
## የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች የተፈቀደላቸው የሥራ መደቦች እና
## በወር የሚያስፈልው የንፅህና መጠበቂያ ዓይነት እና ብዛት

**ሰንጠረዥ 1. የንፅህና መጠበቂያ ቁሳሰቁሶች የተፈቀደላቸው የሥራ መደቦች የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የሚያስፈልው የንፅህና መጠበቂያ አይነት በወር | ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ✓ የጉልበት ሰራተኛ<br>✓ ሁለገብ ጥገና ሰራተኛ | የገላ ሳሙና፤ | 3 |
| | | የልብስ ሳሙና | 4 |
| | | ሶፍት | 3 |
| | | ኤርፍሬሸር | 1 |
| | ✓ ፅዳት | ፀረ-ተባይ | 1 |
| | | የልብስ ሳሙና | 4 |
| | | የገላ ሳሙና፤ | 3 |
| | | ሶፍት | 3 |
| | | ኤርፍሬሸር | 2 |
| 2 | የላውነደሪ /የልብስ እጥበት/ሰራተኛ | የገላ ሳሙና ፤ | 3 |
| | | የልብስ ሳሙና | 3 |
| | | ሶፍት | 2 |
| | | ኤርፍሬሸር | 1 |
| 3 | አትክልተኛ | የገላ ሳሙና | 3 |
| | | የልብስ ሳሙና | 3 |
| | | ሶፍት | 2 |
| | | ኤርፍሬሸር | 1 |
| 4 | የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ፤የንብረት ምዝገባና ቁጥጥር | የገላ ሳሙና፤ | 3 |
| | | የልብስ ሳሙና | 3 |
| | | ሶፍት | 2 |
| | | ኤርፍሬሸር፤ | 1 |
| 5 | ጥበቃ ሰራተኛ | የገላ ሳሙና | 2 |
| | | የልብስ ሳሙና | 2 |
| | | ሶፍት | 2 |
| | | ኤርፍሬሸር፤ | 1 |
| | | ፀረ-ተባይ | 1 |
| 6 | የሰው ሀብት መረጃ ሰራተኛ | የገላ ሳሙና፤ | 2 |
| | | የልብስ ሳሙና | 2 |
| | | ሶፍት | 2 |
| | | ኤርፍሬሸር፤ | 1 |
| 7 | የፎቶ ኮፒና የጥረዛ ሠራተኛ፤የቤተ-መፃህፍት ሰራተኛ፤ ገንዘብ ያዥ፣ ሾፌር፤ ስልክ ኦፕሬር ተላላኪ፤ እንግዳ ተቀባይ፤ ጉዳይ አስፈፃሚ፤ የትራንስፖርት ስምሪት ሰራተኛ/ሃላፊ፤ የግቢ ጥበቃና ውበት ሃላፊ | የገላ ሳሙና፤ | 2 |
| | | የልብስ ሳሙና | 2 |
| | | ሶፍት | 2 |
| | | ኤርፍሬሸር፤ | 1 |
| 8 | ካላይ ከተጠቀሱት የስራ መደቦች ውጭ ያሉ | የገላ ሳሙና ፤ | 2 |

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | የሚያስፈልው የንፅህና መጠበቂያ አይነት በወር | ብዛት |
|---|---|---|---|
| | ሌሎች የተቋሙ ሰራተኞች በሙሉ | የልብስ ሳሙና | 2 |
| | | ሶፍት | 2 |
| | | ኤርፍሬሽር፤ | 1 |
| 9 | ለመካከለኛ የሥራ ሃላፊዎች(ዳይሬክተሮች) | የገላ ሳሙና | 2 |
| | | የልብስ ሳሙና | 2 |
| | | ሶፍት | 3 |
| | | ኤርፍሬሽር | 2 |
| | ለከፍተኛ ሃላፊዎች | የገላ ሳሙና | 3 |
| | | የልብስ ሳሙና | 3 |
| | | ሶፍት | 3 |
| | | ኤርፍሬሽር | 2 |
| 10 | ለአንድ የሥራ ቢሮ የሚያስፈልገው ፀረ-ተባይ | ለከፍተኛ ሃላፊ | 3 |
| | | ለመካከለኛ ሃላፊ | 2 |
| | | በአንድ የሥራ ቢሮ ውስጥ ለሚገኙ ሰራተኞች | 2 |

**ሰንጠረዥ.2. ለአደጋ መከላከያ እና ለደንብ አልባሳት የሚያስፈልግ የጨርቅ መጠን**

| ተ.ቁ | የልብሱ አይነት | መጠን በሜትር |
|---|---|---|
| 1 | ኮትና ሱሪ | 3.50 ሜ |
| 2 | ኮትና ጉርድ ቀሚስ | 3.50 ሜ |
| 3 | ¾ ጋዋን | 2. 70 ሜ |
| 4 | ቱታ | 3.20 ሜ |
| 5 | ሽርጥ | 2.70 ሜ |
| 6 | ፍራሽ | 90 ሳ.ሜ ስፋት |
| 7 | አንሶላ | 1.50 ሜ በ 1.90 ሜ |

**ሰንጠረዥ.3 ስራቸውን ለማከናወን ለፅዳት ሰራተኞች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች**

| ተ.ቁ | የእቃው አይነት | በወርየሚያስፈልገው ብዛት | በሦስት ወር የሚያስፈልገው ብዛት | በአራት ወር የሚያስፈልገው ብዛት | በስድስት የሚያስፈልገው ብዛት | በአመት የሚያስፈልገው ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቡጀዲ | | 1ሜ | | | አራት (4)ሜ |
| 3 | በረኪና3% - 5% ኮንሰንትሬሽን ያለው | 2ሊትር | | | | ሃያአራት (24) ሊትር |
| 4 | ኦሞ | 1ኪ.ግ | | | | አስራሁለት (12) ኪ.ግ |
| 5 | ዲቶል | 1ሊትር | | | | አስራሁለት (12ሊትር) |
| 6 | መጥረጊያ | | አንድ (1) | | | አራት (4) |
| 7 | መወልወያ | | ሁለት (2) | | | ስምንት (8) |
| 8 | ቪም | 2 | | | | 24 |

| ተ.ቁ | የእቃው አይነት | በወርየሚያስ ፈልገው ብዛት | በሦስት ወር የሚያስፈልገ ው ብዛት | በአራት ወር የሚያስፈልገው ብዛት | በስድስት የሚያስፈልገ ው ብዛት | በአመት የሚያስፈልገው ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | ባልዲ | 2 | | | | 24(እንደአስፈላጊነቱ) |
| 10 | የመፀዳጃ ቤት ቡሩሽ | | | | አንድ (1) | በአመት 2 |
| 11 | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ባለ20 ሊትር | | | | | እንደአስፈላጊነቱ |
| 12 | የመስታወት ማፅጃ ኬሚካል | 2ሊትር | | | | ሃያአራት (24) ሊትር |
| 13 | ቆሻሻ ማፈሻ | | | አንድ (1) | | ሶስት (3) |
| 14 | ጣራ መወልወያ (የሸረሪት ድር ማፅጃ (ታጣፊው) | | | | | ስምንት (8) ለሁሉም የሚያገለግል |

## ሰንጠረዥ.4. የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎች የሚያስፈልጋቸው የሥራ መደቦች

| ተ.ቁ | የስራ መደበ | የሚያስፈልገው የአደጋ መከላከያ አይነት | በአመት የሚያስፈልገው ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሴክሬታሪ | ሶላር መነፅር፤ | 1 |
| | | ማፅጃ ፎጣ | 2 |
| | | አልኮል | 3ሊ |
| | | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| 2 | ሾፌር | ሙሉ የስራ ቱታ | 1 |
| | | የደህንነት ቀበቶ፤ | 1 |
| | | የቆዳ እጅ ጓንት | 1 |
| 3 | የሃላፊ ሾፌር | ሙሉ የስራ ቱታ | 1 |
| | | የደህንነት ቀበቶ፤ | 1 |
| | | የቆዳ እጅ ጓንት | 1 |
| 4 | የቤተ መጽሀፍትና ዶክሜንቴሽን ባለሙያ | ¾ ነጭ ጋዋን፤ | 2 |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 3እሽግ |
| | | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | የቤተ-መጽሃፍት ሠራተኛ | ¾ ነጭ ጋዋን፤ | 2 |
| | | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 3እሽግ |
| 5 | የሰው ሃብት አስተዳደር ኃላፊ | ሶላር መነፅር | 1 |
| 6 | የሰው ሃብት አስተዳደር ሠራተኛ እና ባለሙያ | 3/4ጋዋን | 2 |
| | | እጅ ጓንት፤ | 2እሽግ |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 3እሽግ |
| 7 | የሪከርድና ማህደር አገልግሎት ኃላፊ | ¾ ጋዋን፤ | 2 |
| | | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | ሶላር መነፅር | 1 |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፤ | 3እሽግ |

| ተ.ቁ | የስራ መደበ | የሚያስፈልገው የአደጋ መከላከያ አይነት | በአመት የሚያስፈልገው ብዛት |
|---|---|---|---|
| 8 | የሪከርድና ማህደር ሠራተኛ | እጅ ጓንት፤ | 2እሽግ |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፤ | 3እሽግ |
| | | ሶላርመነፅር | 1 |
| | | ¾ ጋዋን | 2 |
| 9 | ሞተረኛ /ፖስተኛ | ሄልሜት ፤ | 2 |
| | | ¾ ጋዋን | 2 |
| | | ጎግል | 1 |
| 10 | ተላላኪ | አጭር ቆዳ ጫማ | 2 |
| | | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| 11 | የፋይናንስ ሃላፊ | ሶላር መነፅር | 1 |
| 12 | ገንዘብ ያዥ፤ረዳት ገንዘብ ያዥ እና ሂሳብ ሰነድ ያዥ | ¾ ጋዋን | 2 |
| | | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 3እሽግ |
| 13 | የግዥና ንብረት አስተዳደር ሃላፊና ቡድን መሪ | ¾ ጋዋን፤ | 2 |
| | | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 3እሽግ |
| | የግዥና ንብረት አስተዳደር ሃላፊ | ሶላር መነፅር | 1 |
| 14 | የንብረት አስተዳደር ሰራተኛና ባለሙያ | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፤ | 3እሽግ |
| | | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | ¾ ጋዋን፤ | 2 |
| 15 | የንብረት ምዝገባና ቁጥጥር ሠራተኛ | ¾ ጋዋን፤ | 2 |
| | | የቆዳ እጅ ጓንት | 2 |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 3እሽግ |
| 16 | የግዥ ሰራተኛ እና ባለሙያ | ¾ ጋዋን፤ | 2 |
| | | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፤ | 2እሽግ |
| 17 | የመረጃ ዴስክ ሠራተኛ | ሶላር መነፅር | 1 |
| | | ኮትና ሱሪ | 2 |
| 18 | ጉዳይ አስፈፃሚ | አጭር ቆዳ ጫማ | 2 |
| | | ኮትና ሱሪ | 2 |
| 19 | ፎቶ ኮፒና ማባዣ ሠራተኛ | የቆዳ እጅ ጓንት | 4 |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ፤ | 2 |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 2እሽግ |
| | | 3/4 ጋዋን | 2 |
| 20 | የስልክ ኦፕሬተር | የፕላስቲክ እጅ ጓንት | 2 |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 2እሽግ |
| 21 | የጽዳት ሠራተኛ | ሙሉ የስራ ልብስ፤ | 2 |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | 2 |
| | | የፀጉር መሸፈኛ ሻሽ | 3 |
| | | ፕላስቲክ የእጅ ጓንት፤ | 4 |

| ተ.ቁ | የስራ መደበ | የሚያስፈልገው የአደጋ መከላከያ አይነት | በአመት የሚያስፈልገው ብዛት |
|---|---|---|---|
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 4 እሽግ |
| 22 | ሁለገብ የጥገና ሠራተኛ | የቆዳ የእጅ ጓንት፤ | 6 |
| | | ጎግል | 2 |
| | | የጆሮ መከላከያ | 2 |
| | | ካልሲ | 4 |
| | | ኬፕ | 1 |
| | | ሙሉ የስራ ቱታ | 2 |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 2እሽግ |
| | | ሴፍቲ ጫማ | 2 |
| 23 | አትክልተኛ | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፤ | 2እሽግ |
| | | ረጅም የቆዳ ጫማ | 2 |
| | | ሙሉ የስራ ቱታ | 2 |
| | | ኬፕ | 2 |
| 24 | የጥበቃ ሰራተኞች ኃላፊ | ኬፕ | 2 |
| | | ካፖርት | 1 |
| | | የዝናብ ልብስ | በ2አመት 1 |
| | | ከጥለት የተሰራ የእጅ ጓንት | 3 |
| | | ኮትና ሱሪ | 2 |
| 25 | የጥበቃ ሠራተኛ | አጭር ቆዳ ጫማ፤ | 2 |
| | | ካፖርት | 2 |
| | | ጃንጥላ | 1 |
| | | የዝናብ ልብስ | 2 አመት 1 |
| | | ከጥለት የተሰራ የእጅ ጓንት | 3 |
| | | ኬፕ | 2 |
| | | ብርድ ልብስ፤ | በ2አመት 1 ለሁሉም |
| | | አንሶላ፤ | በ1አመት 1 ለሁሉም |
| | | ትራስ፤ | በ2አመት 1 ለሁሉም |
| | | ፍራሽ | በ2አመት 1 ለሁሉም |
| | | የእጅ ባትሪ | በአመት 2 ለሁሉም |
| 26 | የምግብ ዝግጅትና የመስተንግዶ አገልግሎት ቡድን መሪ | ነጭ የፀጉር መሸፈኛ ሻሽ | 2 |
| | | ¾ ነጭ ጋዋን፤ | 2 |
| 27 | የምግብ ዝግጅት አገልግሎት ኃላፊ | ነጭ የፀጉር መሸፈኛ ሻሽ | 2 |
| | | ¾ ነጭ ጋዋን፤ | 2 |
| 28 | የምግብና መጠጥ ተቆጣጣሪ | ¾ ነጭ ጋዋን፤ | 2 |
| 29 | የምግብ ዝግጅት ሠራተኛ | ሽርጥ | 3 |
| | | ነጭ የፀጉር መሸፈኛ ሻሽ፤ | 3 |
| 30 | የልምድ አስተናጋጅ | ሽርጥ | 3 |
| | | ነጭ የፀጉር መሸፈኛ ሻሽ፤ | 3 |
| 31 | ባሬስታ | ሽርጥ | 3 |
| | | ¾ ነጭ ጋዋን፤ | 3 |
| 32 | የካፍቴሪያ ገንዘብ ያዥ | የቆዳ እጅ ጓንት | 3 |

| ተ.ቁ | የስራ መደበ | የሚያስፈልገው የአደጋ መከላከያ አይነት | በአመት የሚያስፈልገው ብዛት |
|---|---|---|---|
| | | 3/4 ጋዋን፤ | 2 |
| 33 | የእንግዶች መኝታ ጽዳትና ውበት ሠራተኛ | ሙሉ የስራ ቱታ፤ | 2 |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 3እሽግ |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | 2 |
| | | የፀጉር መሸፈኛ ሻሽ፤ | 3 |
| | | የፕላስቲክ እጅ ጓንት | 3 |
| 34 | እንግዳ ተቀባይ | ኮትና ሱሪ/ሸርጥ/ | 2 |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | 2 |
| | | ባጅ(መታወቂያ) | 1 |
| 35 | የላውንድሪ ሠራተኛ/የልብስ እጥበት/ | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ፤ | 3እሽግ |
| | | ፕላስቲክ ኤፕረን | 2 |
| | | ሙሉ የስራ ቱታ፤ | 2 |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | 2 |
| | | ፕላስቲክ ቡትዝ፤ | 1 |
| | | የፕላስቲክ የእጅ ጓንት | 2 |
| | | ጎግል | 1 |
| 36 | ሲኒየር ሄልዝ ሣይንስ ኘሬፌሽናል (HO) | ጎግል፤፤ | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ሳኒታይዘር | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | አልኮል | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | እጅ ጓንት | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ጫማ | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ሰርጅካል ማስክ | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ሌሎች ለባለሙያው የሚያስፈልጉ ነገሮች | |
| | | ፕላስቲክ ኤፕረን | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ¾ ነጭ ጋዋን፤ | 3 |
| 37 | ክሊኒካል ነርስ | ሳኒታይዘር፤ | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ጎግል | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | እጅጓንት፤ | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ጫማ | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ፕላስቲክ ኤፕረን | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ፕላስቲክ ኤፕረን | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ሌሎች ለባለሙያው የሚያስፈልጉ ነገሮች | |
| | | ¾ ነጭ ጋዋን፤ | 3 |
| 38 | ሜዲካል ላቦራቶሪ ቴክኒሺያን | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ጎግል፤ | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | ሳኒታይዘር | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | አልኮል | እንደአስፈላጊነቱ |
| | | እጅ ጓንት | እንደአስፈላጊነቱ |

| ተ.ቁ | የስራ መደበ | የሚያስፈልገው የአደጋ መከላከያ አይነት | በአመት የሚያስፈልገው ብዛት |
|---|---|---|---|
| | | ሌሎች ለባለሙያው የሚያስፈልጉ ነገሮች | |
| | | ¾ ጋዋን፤፤ | 2 |
| 39 | የህክምና ካርድ ሠራተኛ | የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ | 3እሽግ |
| | | ካፖርት | 2 |
| | | የቆዳ እጅ ጓንት | 3 |
| | | ሶላር መነፅር | 1 |
| 40 | የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | ¾ ጋዋን | 2 |
| | | ሶላር መነፅር፤ | 1 |
| 41 | የህዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ | ¾ ጋዋን | 2 |
| | | ሶላር መነፅር | 1 |
| 42 | የኦዲዮቪዥዋልቴክኒሽያን | ¾ ጋዋን | 2 |
| 43 | የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | ሶላር መነፅር፤ | 1 |
| 44 | የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ባለሙያ | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | ¾ ጋዋን፤ | 2 |
| 45 | የኔትወርክ አድሚኒስትሬተር | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | ሶላር መነፅር | 1 |
| 46 | የዌብሳይት አድሚኒስትሬተር | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | ሶላር መነፅር፤ | 1 |
| 47 | የዳታ ቤዝ አድሚኒስትሬተር | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | ሶላር መነፅር | 1 |
| 48 | ሲስተም አድሚኒስትሬተር | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | ሶላር መነፅር | 1 |
| 49 | ቪዲዮ ኮንፈርንስ ባለሙያ | እጅ ጓንት | 2እሽግ |
| | | ሶላር መነፅር | 1 |

**ሰንጠረዥ.5፡ የደንብና የፕሮቶኮል አልባሳት የተፈቀደላቸዉ የስራ መደቦች እና በአመት የሚሰጣቸው ብዛት**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የጥበቃ ሠራተኛ እና የሽፍት ኃላፊ | ኮትና ሱሪ ለወንድ፣ ኮትና ጉርድ ቀሚስ/ሱሪ ለሴት | በአመት ሁለት |
| | | ሸሚዝ | |
| | | ቀበቶ | |
| | | ክረቫት | |
| | | ካልሲ | በአመት አራት |
| 2 | የወንድ የመልዕክት ሠራተኛ | ኮትና ሱሪ | በአመት ሁለት |
| | | ሸሚዝ | |
| | | ቀበቶ | |
| | | ካልሲ | በአመት አራት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | የሴት የመልዕክት ሠራተኛ | ኮትና ጉርድ ቀሚስ/ሱሪ | በአመት ሁለት |
| | | የውስጥ ልብስ | |
| | | ሸሚዝ | |
| 4 | የወንድ የመረጃ ዴስክ ሠራተኛ | ኮትና ሱሪ | በአመት ሁለት |
| | | ሸሚዝ | |
| | | ቀበቶ | |
| | | ከረቫት | |
| | | አጭር የቆዳ ጫማ | |
| | | ካልሲ | በአመት አራት |
| 5 | የሴት የመረጃ ዴስክ ሠራተኛ | ኮትና ጉርድ ቀሚስ/ሱሪ | በአመት ሁለት |
| | | ሸሚዝ | |
| | | የውስጥ ልብስ | |
| | | ከረቫት | |
| | | አጭር የቆዳ ጫማ | |
| 6 | የፅዳት አስተባባሪ እና የቢሮ ፅዳት ሰራተኛ | ኮትና ጉርድ ቀሚስ/ሱሪ | በዓመት ሁለት |
| | | ሸሚዝ | |
| | | የውስጥ ልብስ | |
| 7 | የመስተንግዶ ሰራተኛ | ኮትና ጉርድ ቀሚስ/ሱሪ | በአመት ሁለት |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | |
| | | ሸሚዝ | |
| | | የውስጥ ልብስ | |
| | | ከረቫት | |
| | | ካልሲ | በአመት አራት |
| 8 | የቢሮ አገልግሎት ሃላፊ | ኮትና ሱሪ | በአመት ሁለት |
| | | ሸሚዝ | |
| | | ቀበቶ | |
| | | ከረቫት | |
| | | ካልሲ | በአመት አራት |
| 9 | የስልክ ኦፕሬተር | ሙሉ ልብስ | በአመት ሁለት |
| | | ሸሚዝ | በአመት ሁለት |
| 10 | የፕሮቶኮል ባለሙያ | የፕሮቶኮል ልብስ | በአመት ሁለት |
| | | ሸሚዝ | |
| | | ከረቫት | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | |
| | | ካልሲ | በአመት አራት |
| | | ኮንጥላ | በሁለት አመት አንድ |
| 10 | የሃላፊና የምክትል ሀላፊ ሾፌር | የፕሮቶኮል ልብስ | በአመት ሁለት |
| | | ሸሚዝ | |
| | | ከረቫት | |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | |
| | | ቀበቶ | |
| | | ካልሲ | በአመት አራት |
| 11 | ሾፌር | ኮትና ሱሪ | 2 |
| | | አጭር ቆዳ ጫማ | 2 |
| | | ሸሚዝ | 2 |
| | | ቀበቶ | 2 |
| | | ካልሲ | 4 |

**ሰንጠረዥ 6፡ በተወሰኑ የሥራ መደቦች ላይ የሚሰሩ ሠራተኞች የተለያዩ ኬሚካሎችና ብናኝ ነገሮች ወደሰውነታቸው ስለሚገቡ የገቡት ኬሚካሎችና ብናኞች ሰውነታቸው ውስጥ ገብተው ለበሽታ ምክንያት እንዳይሆኑ የሚያስፈልግ የወተት መጠን**

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | በቀን የሚያስፈልግ የወተት መጠን በሊትር |
|---|---|---|
| 1 | የፅዳት ሰራተኛ | ½(ግማሽ) |
| 2 | የለውንደሪ/ልብስ እጥበት/ሰራተኛ | ½(ግማሽ) |
| 3 | የፎቶ ኮፒና ጥረዛ ሠራተኛ | ½(ግማሽ) |
| 4 | የንብረት ክፍል አስተዳደር ሠራተኛ | ½(ግማሽ) |

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. መመሪያውን ስለማሻሻል

ከወቅቱ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም ሆኖ ሲገኝ የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ዳይሬክቶሬት አጥንቶ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ አመራር አቅርቦ በማስወሰን መመሪያው እንዲሻሻል ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 18. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በማኔጅመንት ታይቶ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ በዋና ዳይሬክተር አማካይነት ለፍትህ ሚኒስቴር ቀርቦ ተመዝግቦ፣ ቁጥር ተሰጥቶት ዌብሳይት ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

የፌዴራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት

አዲስ አበባ